# ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮለጅ

## የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል


# "የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶና የመስቀል ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር ባህሪያት አንፃር"


**በ**

**ዘላለም ውበቴ**


**ሰኔ 2014 ዓ.ም**

# "የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶና የመስቀል ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር ባህሪያት አንፃር"

በ

ዘላለም   ውበቴ

የጥናቱ አማካሪ

መምህርት ሔለን ገብረስላሴ

ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ የተሠራ ጥናታዊ ጽሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ

የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

## የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩነቨርስቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆነን አረጋግጣለሁ፡፡

የአማካሪዉ ስም ……………………………….

ፊርማ……………………………………….

ይህ በተማሪ ዘላለም ውበቴ "የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶና የመስቀል ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር ባህርያት አንፃር" የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን የዩንቨርስቲዉ ጥራት ደረጃ የሚያሟላና በትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆነን ማረጋገጫ ነዉ፡፡

ፈታኝ አንድ ……………………………..ፊርማ……………………..

ፈታኝ ሁለት……………………………..ፊርማ……………………..
ቀን …………………………

# አበርክቶ

ዘወትር ሲከፋኝ እያፅናኑ ደስታየን እያበዙ  ከገንዘብ እስከ ጉልበታቸው ከልጅነት እስከ ዛሬ ላልተለዩኝ ለውድ እናቴ ለፈንታነሺ ስንሻው እና ለአባቴ ለውበቴ ታደሰ ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

በመጀመሪያ ከጅማሬ እስከ ፍፃሜ ያልተለየኝ ለአምላኬ ለድንግል ማርያል ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ በልጅነት አንደበቴ ምስጋናየን አቀርባለሁ።በመቀጠል ስደክም ብርታቱን፥ስወድቅ ጥንካሬን እየሰጠች ከጎኔ ያልተለየችኝ ለአምላክ እናት ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናየን አቀርባለሁ።ስለቸኝ ደከመኝ ሳትል ስህተቴን እያረመች እና እያማከረች ለዚህ ደረጋ ላድረሰችኝ ለመምህርት ሄለን ገብረሲላሴ ከፍ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ።በተጨማሪም ለንሰሐ አባቴ ለቀሲስ ታረቀኝ አየለ፥ለወላጅ አባቴ ለአቶ ውበቴ ታደሰና ለእናቴ ለፈንታነሺ ስንሻው፥ በመጨረሻም ለጎንጅ ቆለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች፥ወረዳው ለአስተዳዳሪ እና ለቋሪት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች እና ዘወትር በሀሳባቸው፥ ላገዙኝ ጓደኞቼ ይሁንልኝ።

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናታዊ ፁሑፍ ዋና ርዕስ የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ እና የመስቀል ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር ባህርያት አንጻር የሚል ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ ደግሞ የመስቀል እና የለቅሶ ስርአት ምን ይመስላል?የመስቀል በዓል እንዴት ጀመረዉ?የመስቀል እና የለቅሶ ስርአት እንዴትስ ይከዎናል?ምን ባህላዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ አለውን? የሚለውን መመርመር ነው። ከቤተክርስትያን ምን አመስጥሮ አላቸው?መቼ እና እንዴት ይከዎናል?በማህበረሰቡ ኑሮ ላይ ምን ተፅኖ አሳድሯል? የሚሉ ጥያቄዎችን ምላሽ አግኝተዋል።ጥናቱም በዋነኝነት በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ እና ከአጥኝዉ ርዕስ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥናቶች ተቃኝተዋል።

## ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| እዮሃ | እየዋ ታየ |
| ወራንታ | እናቶች የሚሰሩት እቃ |
| እንቆረቆባሽ | እንኳን አደረሰሽ |
| ጭሮ | የጎመን ገለባ |
| ቶፋ | እንስራ |
| ፍንጃል | ስኒ |

## ማውጫ


አበርክቶ ........ I

ምስጋና ........ II

አጠቃሎ ........ III

ሙዳየ ቃላት ........ IV

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሺ ምክንያት ........ 2

1.3 የጥናቱ አላማ ........ 2

1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ ........ 2

1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ ........ 2

1.4 የጥናቱ ዘዴ ........ 2

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3

1.6 የጥናቱ ጥያቄወች ........ 3

1.7 የጥናቱ ወሰን ........ 3

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 3

1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........ 4

2.1 የትውፊት ምንነት ........ 5

2.1.1 የትውፊታዊ ትያትር ባህሪያት ........ 5

2.1.2 የትውፊታዊ ትያትር ጥቅም ........ 6

2.2 የመስቀል ትርጉም ........ 7

2.2.1 የመስቀል ደመራ አጀማመር ........ 7

2.3 የለቅሶ ምንነት ........ 9

ምዕራፍ ሶስት ........ 11

የመረጃ ትንተና ........ 11

3.1 የጎንጅ ቆለላ ወረዳ ታሪካዊ ዳራ ........ 11

3.2 የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ........ 11

3.2.1 ቅድመ ዝግጁት ........ 11

3.2.2 ሬሳ ጠባቂ ........ 11

3.2.3 ግንዘት ........ 12

3.2.4 የሀዘን መርዶ ........ 12

3.2.5 ፍታት ..... 12
3.3 የጎንጂ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ከትዉፊታዊ ትያትር ባህርያት አንጻር ሲተነተን ..... 13
3.3.1 ከመቼት አንጻር ..... 13
3.3.2 ከመዝሙርና ዉዝዋዜ ..... 14
3.3.3 ከተራኪ አንጻር ..... 17
3.3.4 ከመድረክ ቁሳቁስ አንጻር ..... 17
3.3.5 ከገጸ ባህርያት አንጻር ..... 18
3.4 የጎንጂ ቆለላ ወረዳ የመስቀል ስርዓት ..... 18
3.4.1 የመስቀል ባእል ቅድመ ዝግጂት ..... 20
3.4.2 የመስቀል በዓል ደመራ አለኳኮስ ..... 21
3.5 የጎንጅ ቆለላ የመስቀል በዓል ከትዉፊታዊ ትያትር ባህርያት አንጻር ሲፈተሽ ..... 21
3.5.1 ከመቼት አንጻር ..... 21
3.5.2 ከመዝሙርና ዉዝዋዜ አንጻር ..... 21
3.5.3 ከተራኪ አንጻር ..... 23
3.5.4 ከመድረክ ቁሳቁስ አንጻር ..... 23
3.5.5 ከገጸ ባህሪያት አንጻር ..... 24
ምዕራፍ አራት ..... 25
4.ማጠቃለያ ..... 25
ዋቢ መጽሃፍት ..... 27

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ኢትዮጵያ ብዙ ብሔሮችን፡እምነቶችንና ቋንቋወችን በውስጧ አቅፋ የያዘች ሀገር ናት፡በመሆኑም ባሉት ብሔረሰቦች ውስጥ እንደየ እምነታቸው እና ቋንቋቸው መሠረት የተለያየ ባህላዊ ትውፊቶችና ልምዶች በህይወታቸው ያከናውናሉ፡ትውፊት ከጠቃሚ ክንውኖች አንዱ ነው፡፡ትውፊት ከትውልድ ወደ ትዉልድ በሂደት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ጥበብ ነው፡፡ትውፊት የሚለው ቃል"ፓራዶሲስ"ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ነው፡፡የአማረኛ ትርጉሙም አንድን ነገር መስተት ወይም መቀበል፣መረከብ ማለት ነው፡፡ይህም ማለት እምነትን፣ሃይማኖትን፣ቋንቋን፣ስርአትን፣የአኗኗር ዘይቤን ለሚቀጥለው ትውልድ ማስረከብ ወይንም ካለፈው ትውልድ መረከብ ማለት ነው፡፡

ከላይ እንደ ተመለከትነው ትውፊት ካለፈው ትውልድ ተላልፎ የመጣ ነው፡፡ትውፊት የሰው ልጅ የሚያደርገውን እና ያደረገውን ትግል ከቦታ ቦታ ፤ከሃገር ሃገር ያደረገውን ጉዞአወች፤ከተፈጥሮ ጋር ያደረገውን ትግል እና የመሳሰሉትን ጥረቶች እና ውድቀቶች አካቶ ይይዛል፡፡በውስጡ ስርግን፡ለቅሶን፡ዕርቅን፡ባዕል አከባበርንና የመሳሰሉትን ስርዓትች ያካትታል፡፡ ይህም ጥናት ትኩረት አድርጎ የሚያጠናው የጎንጁ ቆለላ ወረዳ ባህል የሆኑትን የለቅሶና መስቀል ስርዓት ክዋኔ ላይ ሲሆንለክዋኔው ድምቀት የሚሰጡ አባባሎችን፡ ስነቃሎችን መመልከትና ስርአቱን ከትውፊታዊ ትያትር ባህሪያት አንፃር ብቻ ይቃኛል፡፡በመቀጠልም ማንኛውም ትውፊት ላይ የሚጠና ጥናት አስፈላጊነቱ እንደነዚህ አይነት ትውፊቶች እንዲዳብሩ ያደርጋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሺ ምክንያት

አጥኝው ይህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች በወረዳው ባህል ላይ ምንም አይነት ጥናት ባለመኖሩ ይህ ጥናት ወረዳውን ብሎም ማህበረሰቡን እንዲሁም በዓሉን ከማስተዋወቅ አንፃር የጎላ ድርሻ ይኖረዋል በማለት እና የወረዳውን የለቅሶ እና የመስቀል ስርዓትን ይበልጥ ለማወቅና ለመመርመር ባሉት ፍላጎቶች ነው።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ "የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶና መስቀል ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር ባህሪያት አንፃር"መተንተን ነው።

### 1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርአት የሚጠቀሟቸውን ቁሳቁሶች መግለጽ፣
- የጎንጅ ቆለላ ወረዳ መስቀል በዓል ወጣቶች በምን መልኩ እንደሚያከብሩት መግለጽ፣
- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ሲከወን ምን አይነት ልብስ እንደሚለበስ መግለጽ።

## 1.4 የጥናቱ ዘዴ

አጥኚው የተለያዩ የጥናት መንገዶችን በመጠቀም አጥንቷል።በዋናነት በገላጭ የምርምር ዘዴ ያጠና ሲሆን ገላጭ የምርምር ዜዴ ደግሞ ሃሳቦችን በመተንተንና በመተርጎም ስለሚያስቀምጥ በዚህ መልኩ አጥንቷል። በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት ታትመው ወይንም ተፅፈው የተቀመጡትን ዶክመንቶች በመመልከትና፣ከባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች ጋር በመነጋገር አጥንቷል።ከዚህ በተጨማሪ ታላላቅ አባቶችን ማለትም የሀገር ሺማግሌወችን ካህናትን በማነጋገር ከዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ጋር የሚገናኙ ጥናታዊ ፅሑፎችን ማለትም ዶክመንት ተደርገው የተቀመጡ ጥናታዊ ፅሑፎችን እና የታተሙ መፅሐፍትን በመመልከት አጥንቷል።

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶና የመስቀል ስርዓት ላይ መጠናቱ

የሚከተሉትን ጠቀሜታወች ይኖሩታል ፡፡

- ✓ የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና የመስቀል ስርአት ምን አይነት ገፅታ እንዳለው ማስተዋወቅ፡
- ✓ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ሌሎች ጥናቶች ስላልተጠኑ ወደፊት እንዲጠኑ ማነሳሳት፡
- ✓ የጎንጅ ቆለላ ወረዳውን የለቅሶና የመስቀል ባዕል ስርዓት ለማወቅ ለሚሹ ሰወች መጠነኛ መረጃ መስጠት ነው፡፡
- ✓ የጎንጅ ቆለላ ወረዳን ባህል የሚያሳይ ጥናት በመሆኑ ለቱሪዝም እድገት ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡
- ✓ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል ባዕል አከባበር እየጠፋ እና እየቀነሰ በመሆኑ እንደ መረጃ ለማስቀመጥ ነው፡፡መስተካከል ያለባቸው አጉል ባህሎች ካሉ እንዲስተካከሉ ማሳየት ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ጥያቄወች

- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ወጣቶች የመስቀልን ባእል እንዴት ያከብሩታል?
- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ በመስቀል ባዕል ወጣቶች የሚናገሩት ስነቃሎች አሉ ወይ?
- በጎንጅ ቆለላ የለቅሶ ስርአት ምን ይመስላል?
- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ አንድ ሰው ሲሞት ምን ምን ነገሮችህ ዩደረጉለታል?
- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ በለቅሶ ወቅት ምን አይነት ልብስ ይለበሳል?ለምን?
- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ክዋኔ የሚነገሩ ስነቃሎች ምን ምን ናቸው?
- በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የተለየ የለቅሶ ስርአት የሚደረግላቸው ሰወች አሉ ወይ?አሉ ከሆነ እነማን ናቸው? ልዩነቱ ምን ነው?

## 1.7 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትውፊታዊ ጥናት ሲሆን ትኩረት አድርጎ የሚያጠናውም ይህም ጥናት የጎንጂ ቆለላ ወረዳን የለቅሶና የመስቀል በዓል ስርዓት ከትውታዊ ትያትር ባህሪያት አንፃር ብቻ ለይቶ ይተነትናል፡፡

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ወይንም የተደራጀ ነው፡፡በምዕራፍ አንድ የመግቢያ ክፍል ሲሆን በውስጡ የሚካተቱ የጥናቱ ዳራ፤የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፤የጥናቱ

አላማ፤የጥናቱ ጠቀሜታ፤የጥናቱ ዘዴ፤የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ጥያቄወች ናቸው፡፡በምዕራፍ ሁለት የትውፊት ምንነት፤የለቅሶ ስነ ስርዓትን፤እና የመስቀል ምንነትን እና የመስቀል ደመራ አጀማመርን፤የትዉፊታዊ ትያትር ምንነትን፤የስነቃል ምንነትን እን የስነቃል ባህሪያትን ይተነትናል፡፡በምዕራፍ ሶስት ደግሞ ዋናው የጥናቱ ክፍል ሲሆን በዋናነት የወረዳውን የለቅሶ ስርዓትን እና የመስቀል ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር ባህርያት አንጻር የሚተነተንበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል በዋናነት የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት አንድ ሰው ሞቶ እስከ ቃብሩ ያሉ ስርዓቶችን ከዚያም ከቃብሩ በኋላ ደግሞ የቀጠሮ ለቅሶ ላይ የሚደረጉ ስርዓቶችን በሰፊው የሚተነትንበት ክፍል ነው፡፡በመስቀል በዓልም የሚደረጉ ስርዓቶችን በሰፊው የሚተነትንበት ነው፡፡በምዕራፍ አራት መጨረሻው ክፍል ሲሆን አጠቃላይ የጥናቱ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች የሚሰጡበት ነው፡፡

## 1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኝው ይህን ጥናት ሲያጠና በርካታ ችግሮች ገጥመውታል፡፡በመስቀል በዓል ዙርያ ምንም አይነት ጥናት አለመጠናቱ እንዴት ማስቀመጥ እንዳለበት ተቸግሮ ነበር፡፡ጥናቱ የሚጠናበት ወረዳ ላይ ዶክመንት ተደርገው የተቀመጡ መረጃወች እጥረት ነበር፡፡ከአካባቢው ባለሙያወች ባህልና ቱሪዝም ሃላፊወች ጋር በነበረው ቃለ መጠይቅ ወረዳው ላይ ዶክመንት ተደርገው የተቀመጡ መረጃወች ባለመኖራቸው የሚፈለገውን መረጃ አለማኘት ነበር፡፡አጥኝው እነኝህን ችግሮች ለመፍታት የራሱን መፍትሔወች ተጠቅሟል፡፡ዋናው እንደ መፍትሄ የሆነው ስለ መስቀል በዓል አጥኝው ባለበት ቤተ ክርስትያናት በመሄድ መጽሃፍትን ተመልክቷል፡፡ቃለ መጠየቁን ለመቅረጽ ስለተቸገረ በስልክ በመስማት በወረቀት በማስፈር አስቀምጧል፡፡አጥኝው ጥናት በሚካሄድበት ቦታ ያደገ በመሆኑ ስርአቱን በማስታወስም አስቀምትጧል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 የትውፊት ምንነት

ትውፊት ማለት ከቅድመ አያት ከአባቶች ከእናቶች የተቀበሉት ስርዓት ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ አጠቃላይ የህይወት ገፅታ የሚያንፀባርቅ ነው።ፋንታሁን እንግዳ"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔወቻቸው"በሚለው መፅሐፊ እንዲህ ይገልፃል።"*ትውፊት ከአለፈው ዘመን ወይንም ከአለፈው ትውልድ የተወረሰና ዘመነኛ ደራሲወች በጥናትና ምርምር የሚማሩት ነው።እምነት ስነቃል።፣አስተሳሰብ እና የመሳሰሉትን ያካትታል።እንደ አጠቃላይ ትውፊት የሚፈጠርን ሳይሆን የሚወረሱትን ያመለክታል።"(1993:58*)

ይህ የሚያስረዳው ትውፊት ማለት መቀበል መረከብ ማለት ነው።ይህም ሲባል በእውን የሚታይ ብቻ ሳይሆን እንደ አጠቃላይ አባቶች በህይወታቸው ውጣ ውረድ ያፈሯቸውን ፈጠራወች እንዲሁም በህይወታቸው አምነው የያዙትን እምነት፣አመለካከት በሙሉ ያጠቃልላል።ትውፊትን በመረከብ ወይንም በቅብብል ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ የሚተላለፍ እንደሆነም ሀሳቡ ያስረዳል።

### 2.1.1 የትውፊታዊ ትያትር ባህሪያት

ትውፊታዊ ትያትር ከአለፈው ወይንም ከቀደመው ትውልድ የተወረሱትን ባህሎች በትያትር አዘገጃጀት ስርዓት መድረክ ላይ ማቅረብ ነው።የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ በሚገልፅ መልኩ ለተመልካች የሚያቀርብ ነው።ይህም የራሱ የሆኑ ባህሪያቶች አሉት።ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው"በሚለው መፅሐፉ ባህሪያቶቹን እንዲህ ገልጿቸዋል።

በመጀመሪያ የምንመለከተው ባህሪ ትውፊታዊ ትያትር የሚቀርበው በገላጣ ስፍራወች ነው።መቸት የምንለው ነው።ይህ ማለት ትውፊታዊ ትያትር እንደ መደበኛ ትያትር በጠባብ ቦታ ላይ ለማቅረብ አንችልም።የሚያሳትፋቸው ገፀ ባህሪያት ብዛት ያላቸው በመሆናቸው እንደፈለጋቸው ተንቀሳቅሰው ለመስራት ይመች ዘንድ ገላጣ ስፍራ ይኖረዋል።ይህም ማለት ለትውፊታዊ ትያትር መከወኛ የራሱ የሆነ የተዘጋጀለት ቦታ አለው ማለት ነው።በሁለተኛ የምናየው ዋነኛው ባህሪ ትውፊታዊ ትያትር በመዝሙርና ውዝዋዜ ታጅቦ ይቀርባል።ይህ ማለት እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደየ ትውፊቱ ባህሉን ወጉን ስርዓቱን የሚገልፅበት የራሱ የሆነ

መዝሙርና ውዝዋዜ አለው::ትውፊታዊ ትያትርም የአንድን ማህበረሰብ የህይወትገፅታ እንደ ማሳየቱ መጠን ለሚያሳየው ትውፊት መዝሙርና ውዝዋዜ ይኖረዋል::

ሶስተኛው ደግሞ ቁርጥራጭ ትዕይንቶችን የሚያገናኝ ተራኪ አለው::በትውፊታዊ ትያትር ስለቦታው መገኛ እና ስፋት ስለማህበረሰቡ ቋንቋ፣ እምነት በአጠቃላይ ባህሉን ለተመልካች ግልፅ ይሆን ዘንድ የተራኪ ገፀ ባህሪ አለው::አብዛኛወች የትፊታዊ ቲያትር ፅሑፎች ተቆራርጠው የተፃፉ ስለሆኑ ተራኪው እንደ ድልድይ በመሆን ያለፈውን ከአሁኑ ጋር እያዛመደ ትያትሩ በቅደም ተከተል እንዲጓዝ የሚያደርግ ነው::አራተኛው ትውፊታዊ ትያትር ጥቅም ላይ የሚውሉት የመድረክ ቁሳቁሶች ባህላዊ ዕቃወች ናቸው::ትውፊታዊ ትያትር በሚሰራበት ጊዜ በርካታ ቁሳቁሶችን ይጠቀማል::የሚቀርበው ቴአትር የማህበረሰቡን ማንነት የሚገልፅ ስለሆነ ቁሳቁሶችም ባህሉንና ትውፊቱን የሚገልፁ ናቸው::ለምሳሌ:-ከበሮ፥ጥሩንባና የመሳሰሉት ናቸው::

አምስተኛው ገፀ ባህሪያቶች ናቸው::አስተኔ እና ወጥ ብለን እንከፍላቸዋለን አስተኔ ስንል ልክ እንደ ወጥ ገፀ ባህሪያት በአራቱም የገፀ ባህሪያት አሳሳል ሊሳሉ የማያስገድዱ ገፀ ባህሪያት ናቸው::በአራቱ የገፀ ባህሪያት ስንል አሳሳሎች በአካላዊ፣በማህበራዊ፣በስነ ልቦናዊ፣ በሞራላዊ አሳሳል ላይሳሉ ይችላሉ::በዚህም አብዛኃወቹ አስተኔ ገጸ ባህርያት ናቸው:: ደበበ ሰይፉ "የትያትር ጥበብ"በተሰኘው መፅሐፉ ስለ አስተኔ ገፀ ባህሪያት እንዲህ ያብራራል::*"አስተኔ ገፀ ባህሪያት የባህሪ ውስብስብነት የማይታይባቸው ተደራሲያኑ በመድረክ ላይ እንዳገኛቸው በቀላሉ ሊያውቁ የሚችሏቸው ገፀ ባህሪያት ናቸው::"(1973፡32)*

ይህ ማለት አስተኔ ገጸ ባህርያት ማንነታቸውን ማለትም የዋህነታቸውን፣ክፋታቸውን፣ቂም መያዛቸውን፣ለሰው ያላቸውን አመለካከቶች በሙሉ ምንም ሳያስቸግር ማወቅ እንችላለን ማለት ነው::በአጠቃላይ ትውፊታዊ ትያትር በማስመሠል የሚሰራ ስለሆነ እያንዳንዱ ስራወች ትውፊቱን የሚገልፁ፥ትውፊቱ የነበረበት ጊዜውን የሚዋጁ መሆን ይኖርባቸዋል ማለት ነው::

## 2.1.2 የትውታዊ ትያትር ጥቅም

ትውፊታዊ ትያትርን አብዛኛው ሰው እንደ መዝናኛ ይጠቀመዋል::ይህ ማለት አያዝናናም ሳይሆን ሌሎች በርካታ አጥቅሞች ይኖሩታል::ይህም ሲባል ከማዝናናት በተጨማሪ ስለ ትውፊቱ ግንዛቤ ለመፍጠርም ነው::አበበ ማስረሻ በ2012ዓም "የወገራ ወረዳ ፉከራ ከትውፊታዊ ትያትር አላባውያን አንፃር"በሚል በሰራው ጥናቱ ስለ ትውፊታዊ ትያትር ጥቅም

እንዲህ ይገልፃል።ትውፊታዊ ትያትር በአንድ አካባቢ ብቻ ተወስነው የተቀመጡ ባህሎችን ለሌላው ማህበረሰብ ክፍል ያስተዋውቃል(2012:9)።ይህ ማለት አንድ ማህበረሰብ የራሱ ባህል እንዳለ እንጅ የሌላ ማህበረሰብ ባህል መኖሩን አያቅም።ስለዚህ ለእንደዚህ አይነት ማህበረሰቦች የእነሱን ባህል ለሌላ የሌላውን ደግሞ ለነሱ የማስተዋወቅ ጠቀሜታ አለው።

ትውፊታዊ ትያትር ማህበረሰቡን ከማዝናናት ውጭ የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ፣ህፀፁን መልሶ ለራሱ ያሳያል።በዚህም ጥንካሬያቸውን እንዲያዩና ድክመታቸውን ተመልክተው እንዲማሩ በማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው።(2012:9) አንድ ማህበረሰብ ከአያት ከቅደመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በርካታ ትውፊቶችን ይይዛል።ስለዚህም ከተቀበሉት ትውፊት እያከናወኑት እየጎዳቸው የሚጠቅም መስሏቸው እያካሔዱ ያለውን በትያትር መልክ እንደ ትምህርት መስጠትና መልካም ነገሮች ደግሞ የተረሱም ካሉ እንዲቀጥሉና ለወደፊቱ ትውልድም በጥንቃቄ እንዲያስተላልፉ ዋናውን ሚና ይጫወታል።

## 2.2 የመስቀል ትርጉም

መስቀል በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ተብሎ ይጠራል።መስቀል ሰቀለ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም መስቀያ ወይን መከራ ማለት ነው።መምህር ፍቅረማርያም አስማማው መፅሓፈ ታሪክ በተሰኘው መጽሃፋቸው መስቀል ጌታችን መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል በቀራንዮ አደባባይ የተሰቀለበት ነው በማለት ገልጸዋል።ስለዚህ መስቀል ማለት መሰቀያ ማለት ሲሆን በክርስትና እምነት አማኞች ዘንድ መስቀል መድሃኒት ነው በማለትም ያከብሩታል።መድሃኒት ያሉበት ምክንያትም እየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞትን ሽሮ ከፍርድ ወደ ምህረት አሽጋግሯል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

### 2.2.1 የመስቀል ደመራ አጀማመር

በክርስትና እምነት ተከታዮች እየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ተሰቅሎ ሞትን ድል ካደረገ በኋላ መስቀል የበሺተኞች ፈውስ በገሀድ እንደታየ ይታመናል። በዚህም አይሁዳውያን መስቀሉ በሽተኛ ሲፈውስ፣ህሙማንን ሲያድን፣አንካሳወችን ሲጠግን ተመልክተው ክርስቲያኖች በመስቀል እንዳያምኑ ለማድረግና መስቀሉ ድህነት በመስጠቱ ቀንተው ከክርስቲያኖች እይታ ለመሰወር ጉድጓድ ቆፍረው ቀበሩት።መምህር ፍቅረማርያም

አስማማው"መፅሐፈ ታሪክ"በሚለው መፅሐፋቸው ስለ ደመራው አጀማመር እንዲህ ገልፀውታል፡፡

*ንግስት ዕሌኒ ወንድ ልጅ ወልጆ ክርስቲያን የሆነ እንደሆነ የነገሰም*

*እንደሆነ የተሰቀልክበትን ዕፀ መስቀል ከተደበቀበት ቦታ ፈልጌ*

*አውጥቼ ለክርስቲያኖች አብነት አሰፈስቀምጣለሁ ብላ ስዕለት*

*ተስላ ነበርና ያሰበችው ብስዕለት ደርሶላት ወደ እየሩሳሌም*

*ሒዳ አንድ የአይሁድ ወገን የሆነ ኪራኮስ የሚባል ሰው አግኝታ*

*በጠየቀች አልናገርም አላውቅም ቢላት ጨው የበዛበት ምግብ*

*አበላችውና ውሀ ከልክላው ውሐ ለማግኘት ሲል የተቀበረበት*

*አካባቢ ሶስት ኮረብቶች ጠቆማት እሷም ከኮረብቶች አካባቢ*

*ደመራ አስደምራ እጣን ጨምራ ደመራውን አቀጣጠለችው፡፡*

*የእጣኑ ጭስ ወደ ሰማይ ወጥቶ ተመልሶ መስቀሉ ካለበት*

*ኮረብታ ላይ አረፈ፡፡ንግስት ዕሌኒ በእምነት መስከረም 17*

*ቀን ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 ቀን መስቀሉ ተገኝቷል፡፡*

*በዚህም ቁፋሮ በተጀመረበት በመስከረም 17 በየ አመቱ*

*የደመራ ቀን ሆኖ እንዲከበር መጋቢት 10 በተገኘበት*

*የመስቀሉ መታሰቢያ ቀን ሆኖ ይከበራል፡፡(1999:43)*

በዚህም በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በደማቅ ሁኔታ የሚከበር መስከረም 17 ቀን ነው፡፡ቀኑ በክርስትና እምነት የድህነት ቀን፥የፍቅር ቀን፥የአንድነት ቀን ተብሎ ይጠራል፡፡ ምክንያቱም ድህነት የተባለበት አንድም በመስቀሉ ፈውስ አለ፤በመስቀሉ ብርሀን አለ፤በመስቀሉ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ታይቶበታል፡፡ሊቀ መዘምራን ላዕኪ ማርያም ወልደ እየሱስ"መፅሐፈ ሰንክሳር"በተባለው ታላቅ መፅሐፋቸው ስለ ባዕሉ እንዲህ ገልፀዋል፡፡"የዓዲቁ

ንጉስ የቆስጠንጢንዮስ እናት ንግስት ዕሌኒ መስቀሉ ከተሰወረበት የገለጠችበት ቀን ነው"(2007:79)በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.3 የለቅሶ ምንነት

ለቅሶ ማለት ሃዘን ማለት ነው፡፡እንባ በማፍሰስ የሚታዘን ሃዘን ማለት ነው፡፡ይህ ማለት ሰው ሲሞት፣በግል በሚመጡ ሃሳቦች፣አዳጋ ሲደርስበት እንባውን በማፍሰስ የሚያለቅሰው ወይም የሚያዝነው ሃዘን ነው፡፡አንድ ሰው ብቻውን ሆኖ ቢተክዝ ወይንም ቢያዝን ለቅሶ አንለውም፡፡እንባ በማፍሰስ ካለቀሰ ደጎ አለቀሰ እንለዋለን፡፡ለቅሶ አብዛኛው ማህበረሰብ ሰው ሲሞትበት ሃዘኑን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡የተወሰነው ደግሞ የራሱ ስሜት ሲሰማውም ያለቅሳል፡፡ስለዚህ በአጠቃላይ ለቅሶ ማለት ንባ በማፍሰስ የተሰማን ሲሜት መግለጫ ማለት ነው፡፡

## 2.4 የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት

አጥኝው ይህን ጥናት በሚያጠናበት ወቅት ባህሎች ከትውፊት አንፃር የተሰሩ ጥናቶችን በመመልከት አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን ተመልክቷል፡፡

ኤሊያስ ወላንሳ በ2006ዓም "ባህላዊ የግጭት አፈታት እና ስርዓት በሀላባ ብሔረሰብ"በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን ርዕሳቸው የተለያዩ ቢሆንም ተመሳሳይነትም አላቸው፡፡ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳሳይነት ሁለቱም ባህል ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ በአራቱም ምዕራፎች የተዋቀሩ መሆናቸው፤ይህም ማለት በምዕራፍ አንድ የመግቢያ ክፍል የጥናቱ ዳራ፣ጠቀሜታ፣አላማ፣እና ዘዴ፤በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የለቅሶ ምንነት፣የትውፊት ምንነትን የቃኘ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የለቅሶ ስርአት ትንተና ላይ ብቻ ይመሳሰላሉ፡፡ በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ አ ንድ አይነት ናቸው፡፡ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የቦታ ልዩነት ይህም ማለት የኤሊያስ ጥናታዊ ፅሑፍ ሀላባ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነው፡፡ ይህ ጥናት የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓትና መስቀል ስርዓት ላይ ያጠነጠነ ሲሆን የኤሊያስ ጥናት ደግሞ የሀላባ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ላይ ያጠናል፡፡

አበበ ማስረሻ በ 2012ዓ.ም “የወገራ ወርዳ ፉከራ ከትውፊታዊ ትያትር አላባውያን አንፃር” በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበት ሁለቱም ባህል ላይ ያተኮሩ መሆናቸው፣በአራቱም ምዕራፎች የተዋቀሩ መሆናቸው ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ የመግቢያ ክፍል የጥናቱ ዳራ፣ጠቀሜታ፣አላማ፣እና ሌሎችም፤በምዕራፍ ሁለት የትውፊት ምንነት እና ጠቀመታዎች፤ ዕራፍ ሶስት ደግሞ ትንተና ክፍል በመሆን ይመሳሰላሉ፡፡ልዩነታቸውን ስንመለከት የአበበ ጥናታዊ ፅሑፍ ፉከራ ላይ ብቻ ያጠነጠነ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ደግም ለቅሶና መስቀል ስርአትን የሚቃኝ ነው፡፡ሌላው ቦታቸውም የተለያዩ ናቸው፡፡የአበበ ጥናት ወገራ ወረዳ ሲሆን ዬህ ጥናት ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የመረጃ ትንተና

### 3.1 የጎንጅ ቆለላ ወረዳ ታሪካዊ ዳራ

ጎንጅ ቆለላ ወረዳ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ 17 ወረዳወች አንዱ ሲሆን ከባህርዳር ከተማ በ7 ኪሎ ሜትር ርቀት ትገኛለች።በሰሜን ከአንዳቤትወረዳ፣በደቡብ ከቋሪት ወይም ቢቡኝ ወረዳ፣በምስራቅ አዴት ወረዳ  በምዕራብ ሞጣ ያዋስኗታል።ወረዳው በውስጡ 7 ከተማ እና 29 ቀበሌወችን በውስጡ  የያዘ ሲሆን 1350584 የሚሆን ህዝብ አላት። የማህበረሰቡ የኢኮኖሚ ሁኔታ የተመሠረተው በግብርና እና ከብት ርባታ ላይ ነው። መልከአምድራዊ አቀማመጥ ስንመለከት የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የልማት እቅድ ዝግጅት ግምገማ ቡድን መሪ የሆኑት አቶ አቢዮት በላይነው እንዲህ ገልፀውታል።"75%ሜዳማ:9%ተራራማ፡ 16% ወጣ ገባማ ሲሆን አየር ንብረቱም 43%ወይና ደጋ:57%ቆላማ" መሆኑን ገልፀዋል። የማህበረሰቡ የስራ ቋንቋ አማርኛ ብቻ ሲሆን የራሱ የሆኑ የአለባበስ እና የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የለቅሶና የመሥቀል ስርዓቶች ናቸው።

### 3.2 የጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት

#### 3.2.1 ቅድመ  ዝግጂት

በወረዳው አንድ ሰው ይሞታል ተብሎ ከተገመተ የሚዘጋጁ ዝግጂቶች አሉ፡ለሚች መገነዣ አቡጀዲ፣ሰሌን፣መግዛት፡ንስሐ አባት ለሁለት ሳምንታት ቁጭ ብለው ይጠብቃሉ።ይህም ምክንያቱ ሚች ባለፈው ህይወቱ የሰራውን ሀጢያት እንዲናዘዝና የሚቻል ከሆነ እንዲቆርብ ይደረጋል።በተጨማሪ ሀብትና ንብረት ያለው ከሆነ እንዲናዘዝና ንስሐ አባተ ሌላ ጊዚ እኩል እንዲካፈሉ በወረቀት የተፃፈውን በማንበብ ሀብቱን እኩል ያካፍላሉ።

#### 3.2.2 ሬሳ ጠባቂ

በወረዳው ሬሳውን ለመጠበቅ የሚመረጡ ሰወች ንቁና ደፍረት ያላቸው ናቸው።ሰው ሲሞት አይኑን ስለማይዘጋ አይኑን እንዲዘጉ እና የሚችን ሰውነት ለግነዛ እንዳያስቸግር ሰብስበው የሚያስቀምጡ ናቸው።የሩቅ ዘመድ እስኪመጣም ይጠብቃሉ።

### 3.2.3 ግንዘት

በወረዳው አብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታዮች ስለሆኑ የግነዛ ስርዓቱ የፍታት ፀሎት ስርዓት ከተደረሰ በሗላ ነው፡፡ከመገነዙ በፊት ሬሳው በውሀና በወይራ ቅጠል ይታጠባል፡፡ለምን በወይራ ቅጠል ይታጠባል ለሚለው ጥያቄ በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የቅ/ገብርኤል ቤተክርስቲያን አገልጋይ ቀሲስ ታረቀኝ አየለ እንዲህ ገልፀዋል፡፡"ወይራ ቅጠል በክርስትና እምነት ምህረት ነው፡፡በዚህም በኖህ ዘመን ምድርን ለአርባ አመታት በውሀ መጥለቅለቅ በጠፉች ጊዜ ኖህና ዘመዶች መርከብ ውስጥ ተቀምጠው በ40ኛ አመት ኖህ ርግብን ውሀው መጉደሉን አይተሺ ነይ ብሎ በላካት ጊዜ ውሀው መጉደሉን ለመግለፅ የወይሯ ቅጠል አምጣለች፡፡በዚህም መሠረት ከሞት በሗላ ትንሳኤ ወይም ህይወት እንዳለ የሬሳው መታጠብ ይገልፃል፡፡"በማለት ገልጸዋል፡፡

ቤተ ቤተክርስቲያን ሲገባ በንፅህና መግባትም ስላለበት ነው፡፡የሚገንዙ ሰወች እድሜያቸው ከ50 አመት በላይ የሆኑ ናቸው፡፡ሟች ሲገነዝ ቄስ ከሆነ እጁን አጣምሮ ደረቱ ላይ መስቀል ይደረጋል፡ምዕመን እጁን አጣምሮ ብልቱ ላይ ይደረጋል፡መነኩሴ ከሆነ እጁን አጣምሮ አይኑ ላይ ይደረጋል፡፡ቀሲስ ታረቀኝ አየለ ምክንያቶቹን እንዲህ ገልፀዋል፡፡"ካህን ክህነቱን ለመ ግለፅ ነው፡፡ም ዕመ ን ደግሞ  በአንድ ሚ ስት/ባል መ ወሰኑን ለመ ግለፅ ሲሆን መ ነኩሴ ደግሞ አለምን ትቻታለሁ ከሷ የሚታየውን አላይም ሲል ነው፡፡"

### 3.2.4 የሀዘን መርዶ

በዚህ ወረዳ ሰው ሲሞት በሌላ ቀበሌ ወይም አካባቢ ለሚኖሩ ሰውች የሀዘን መርዶ የሚነገረው በጩኸት ነው፡፡የሚጮኸው ከሌሊቱ 11 ሰአት ጀምሮ ነው፡፡ጧሒ ጥሩንባ እየነፋ"አቶ እገሌ እገሌ አርፌዋልና አቃብሩኝ ተብላችሗል ውው ወዉ ውው"እያለ  ያረዳል፡፡ ወጣት ከሆነ ማለትም በማህበረሰቡ ብዙም ያልታወቀ ከሆነ ደግሞ በሰውየው ስም"የእገሌ እገል ልጅ አርፏልና አቃብሩኝ ተብላችሗል ውው...ውው..ውው"በማለት ያረዳል፡፡መርዶ የተነገራቸው ሰወች ሴቶች ጥቁር ልብስ ከሌለ ወደ ጥቁር የተቀራረበ ለብሰው ወገብ ላይ ዘቅዝቀው አስረው ለኂላ ለእዝኑ ጠላ አድርገው፡ወጥ ሰርተው ሁሉን አዘጋጂተው ይሔዳሉ፡፡ከቀበሩ በሗላ መጥተው ይወስዱታል፡፡ወንዶችም ጥቁር  ልብስ ለብሰው ይሔዳሉ፡፡

### 3.2.5 ፍታት

ፍታት በክርስትና እምነት ተከታዮች የሚታመን አንድ ሰው ሲሞት የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ይህም ጸሎት የሞተው ሰው በሃጥያት ታስሮ ወይንም ሃጥያት ካለበት አምላኩ ይቅር

ይለው ዘንድ ካህናት የሚያደርጉለት ጸሎት ነው።በክርስትና ሃይማኖት ዘንድ ቄስ ወይንም ካህን የክርስቶስ ያምላካቸውን ትእዛዝ የሚጠብቅ ሃጥያት የሚያሳርጉ ተብለው ስለ ሚታመኑ በሒወት ንስሃ በመስጠት እንደሚፈቱ ለሞተ ሰውም እንዲሁ ፍታት ጸሎት ያደርጉለታል። ይህም ጸሎት ሲደረግ የፍታት ጸሎት እንለዋለን።በወረዳው ሰው ሲሞት ሰባት ጊዜ የፍታት ፀሎት ይደረጋል።ምክንያቱ ደግሞ አንድ ክርስቲያን በቀን ሰባት ጊዜ መፀለይ አለበት ስለሚል ነው።ከቤት ጀምሮ በየ ጥላው በሚያርፍበት ቦታ ፍታት እየተደረገለት ይሔዳል።በፍታት ጊዜ ከበሮ፡ፅናፅል፡መቋሚያ፡ፅንዓ እና የካህን አልባሳትን ይጠቀማሉ።

ቤተክርስቲያን ከደረሰ በኋላ የአስከሬን ተሸካሚወች ሟቹን ከፍ ዝግ በማድረግ ቤተ ክርስቲያን ያሳልሙታል።ምክንያቱም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ለክርስቶስ ቤት መስገድ አለበት። ካህናቱ የመጨረሻውን የፍታት ፀሎት ካደረጉ በኋላ ጉድጓዱን ያጥኑታል ፀበልም ይረጩታል። አልቃሺና አስለቃሺ ደግሞ ከሰው መሐል ሆነው አስለቃሺ ድምፁን ከፍ አድርጎ የሙሾ ግጥም ይደረድራል።ሌላው ፀጥ ብሎ ይሰማል።የሙሾ ድርደራው ሲያልቅ የሴቶች ደረት ድቂ ይጀምራል።ድብልቅልቅ ይላል።አስከሬኑን እግሩን ወደ ምስራቅ ራሱን ወደ ምዕራብ በማድረግ ይቀብሩታል።ለዚህም ምክንያት ደግሞ ከሞት በኋላ በብርሀን ይነሳል ተብሎ ይታመናል። ምስራቅ በክርስትና አማኞች ዘንድ ብርሃን ናት።ቃብሩ ካለቀ በኋላ አባቶች የቀጠሮ ለቅሶ ቀን ያስይዛሉ።ቢረዝም ሁለት ወር ይቆያል።እስከ 40 ቀን ጧት ጧት 12:00 ሰዓት እየተሔደ መቃብሩጋ ይለቀሳል።ይህም የራሳቸው የሃእን ጉዳትና የሞተው ሰው በጣም ማዘናቸውን ለመግለጽ ነው።በ3ቱ፤በ7ቱ፤በ12ቱ፤በ30፤በ40ው እየተባለ ቅዳሴ እየተቀደሰ ፊታት ይደረጋል። ይህ በወረዳው ማህበረሰብ ነፍስ ይማር ማለት ነው።ለነፍስ ይማርም ለካህናቱ እንጀራ በውት እና ጠላ ይመጣላቸዋል።

## 3.3 የጎንጂ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ከትዉፊታዊ ትያትር ባህርያት አንጻር ሲተነተን

### 3.3.1 ከመቼት አንጻር

በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት የሚከወንበት የራሱ የሆነ ሰፋፊ እና ገላጣ ስፍራወቺ ወይም ቦታወች አሉ።አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የሟች ቤት ጠባብ ከሆነ ጎረቤት ጋ በመውሰድ ሰፋ ያለ ቦታ ስርዓቱ እንዲፈጸም ይደረጋል።ሬሳው መንገድ ላይ ሲወጣም መንገድ ላይ ሁሉም ሰው ቦታ ቦታ ይዞ ቆሞ የፍታት ጸሎት ሲደረግ፣ቤተ ዘመዱ ከሩቅ ቦታ እየመጣ

ሲቀላልቀል ያለው ስርዓት ለየት ያለ በመሆኑ ሰፋ ያለ ቦታ ያስፈልገዋል።ቤተክርስትያን ከተደረሰ በኋላም ስርዓተ ቀብሩ ከመፈጸሙ በፊትም ወዳጅ ዘመድ ተሰልፎ እና ክብ ሰርቶ የሚቆምበት እና የሚያለቅስበት፣ አስለቃሽ ከመሃል ሆኖ የሚያስለቅስበት ስርዓት፣ካህናትም ሁሉም ጎን ጎን ተሰልፈው የፍታት ጸሎት የሚያደርጉበትም ለየት እና ሰፋ ያለ ቦታ ያስፈልጋል።ግብአተ መሬት ወይንም ቃብሩ ላይ ደግሞ አፈር ለማልበስ የመጣው ሰው እና ሃዘንተኛ ተከትሎ የመጣው ሰው ብሎም ያገርተኛ ሰው ጥግ ጥጉን ይዘው የቤተ ዘመዱን አልለቃቀስ በትዝብት የሚያይበት፣በመጨረሻም ከቃብሩ በኋላ ቃብሩ ቦታ ላይ የሚደረገው የሴቶች የደረት ድቂ ስላለ ሰፋ ያለ ቦታ ያስፈልጋል።

አቶ መዘመር ቻሌ ታደሰ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የቅዱስ ገብርኤል ቀበሌ ነዋሪ ስለ ቦታው ሲፋት እና ጥበት ሁኔታ እንዲህ ስይገልጻሉ።"በለቅሶ ስርዓታችን በጣም ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ የቦታ ስፋት መኖር ነው።ምክንያቱም ገና ከቤት ጀምሮ ሰው ሞተ ከተባለ ሁሉ ይጠራራል ብዙ ሰው ይሆናል።ቃብሩ ላይም የሟች ዘመድ በምንቀብርበት ሰዓት ጉድጓዱጋ እኤ ካልገባሁ እያለ የሚገለገልበት ስላለ ሰፊ ቦታ ስለሚያስፈልግ ራሱን የቻለ የለቅሶ መለቀሻ ቦታ አለን።"በማለት ገልጸዋል።ከቀብር መልስም እዝን ወይንም የነፍስ ይማር ሲበላ ሰፋ ያለ ሜዳ ላይ ነው።ስለዚህ በአጠቃላይ በለቅሶ ስርአት ራሱን የቻለ የማስለቀሻ እና የመለቀሻ ሰፋ ያለ ቦታ አላቸው።

### 3.3.2 ከመዝሙርና ዉዝዋዜ

ትዉፊታዊ ትያትር በአብዛኛ ው በመዝሙርና ዉዝዋዜ የታጀበ እና የደመቀ ነው።በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርአትእንዲሁ በመዝሙር እና ዉዝዋዜ ወይንም በዜማ እና እንቅስቃሴ የታጀበ ትዉፊታዊ ክዋኔ አለው።ወንዶች በሚያሳዝን የቀረርቶ ዜማ እና ፉከራ የሟችን ስም በማወደስ እና በማስታወስ ሃዘናቸውን ይገልጻሉ።ሴቶች ደግሞ በደረት መድቃት ክዋኔ ጊዜ ጎንበስ ቀና እያሉ በአንድ አይነት ዜማ 'ው ው" በማለት ሃዘናቸውን ይገልጻሉ።ደረት ድቂው ላይ አንድ ሴት "ዉ ዉ"ስትል ሌሎች ደግሞ በመቀበል በአንድ አይነት ዜማ "ው ው"በማለት እየተቀባበሉ የለቅሶውን ክዋኔውን ያደምቁታል።ሴቶች በማስለቀስም ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በሚያሳዝን የእንጉጉሮ ዜማ ያስለቅሳሉ።ወንዶችም እንዲሁ የተለያሁ ስነቃሎችን በመደርደር በፍከራ እና በቀረርቶ ሃዘናቸውን ይገልጻሉ።ስነቃሎች እንደየ ሟቹ ሰው ይለያያሉ።በለቅሶ፣ በፍከራ እና በቀረርቶ ጊዜ የሚነገሩትን ስነቃሎች አሉ።ወጣት በሚሞትበት ሰዓት እንዲህ በማለት ይገልጻሉ።

አስለቃሽ፦ምን አለ ብተወው አበባው ቢበስል፣

ካንተ በላይ ዳኛ ያለብህ ይመስል፡፡

አልቃሽ፦ እኔን እኔን እኔን

በማለት ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ሴቶች ስነቃሉ ተነግሮ ወይንም ተደርድሮ ሲያልቅ “ው ው ው”በማለት ደረት በመድቃት ጎንበስ ቀና በማለት ያለቅሳሉ፡፡ዝም ሲሉም ባንዴ ዝም ይላሉ፡፡ከዛ ስነቃሉ ይቀጥላል፡፡ትልቅ ሰው ሲሞትም ስነቃሉን እንዲህ በመደርደር ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡

አስለቃሽ፦ ከዘንድሮ ራብ የከርሞው ይብሳል፣

በሬ በሬው ሞቶ በምን ዱታረሳል፡፡

አልቃሽ፦እህህ እኔን እኔን ...እያሉ ታላቅነቱን ይገልጻሉ፡፡በሌላ በኩል የልጅ አባት ከሆነ ደግሞ እንዲህ በማለት ስነቃል ዱደረድራሉ፡፡

አስለቃሽ፦ እረ ተው ተመለስ ሰው ይፈርድብሃል፣

እኒያ ልጆችህን ጅብ ይበላብሃል፡፡

አልቃሽ፦እኔን እኔን እኔን… በማለት ሃዘናቸውን ዱገልጻሉ፡፡

አስለቃሽ፦በጠፍጣፋ ድንጋይ ከተዘጋ በሩ፣

እናት አትገኝም እንደወፍ ቢበሩ፡፡

አልቃሽ፦ እኔን እኔን እኔን…በማለት የልጆች እናት መሞቷን ዱገልጻሉ፡፡

ሴቶች በየ ስነቃል መሃል ላይ የደረት ድቂው የተጠበቀ ነው፡፡ደረት ድቂ ለለቅሶው ክዋኔ ዋናው ድምቀት ነው፡፡በተጨማሪም ደረት ሲደቃ በኋላ ህመም አለው፣ይህም ማለት የሞተው ሰው ወደፊትም ይቆረቁራል ማለት ነው፡፡ማስለቀስ የሚችል ሴት ካለ እየገባ ማስለቀስ ይችላል፡፡ ስነቃሉ ከወንዶች የተለየ ነገር የለውም እንደ ወንዶች የሚቹን ማንነት መግለጽ የሚችሉና ሃዘናቸውን መግለጽ የሚችል ነው፡፡ሌላው ፍከራና ቀረርቶ ለወንዶች ብቻ ስለሆነ ሴቶቹ ዳር ዳር ይዘው በመቆም ስነቃሉ እና ፍከራውን ብሎም ቀረርቶውን በዝምታ ይሰማሉ፡፡በባህላቸው መሰረት ሴት ልጅ አታቅራራም እናም አትፎክርም፡፡ለመፎከርያ ቦታ ሰፋ ተደርጎ ይከፈትና

አቅራሪው ይጀምራል።በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት መሰረት ፍከራና ቀረርቶ የሚኖረው የሞተው ሰው ትልቅ ከሆነ ብቻ ነው።ቢያንስ ከ 45 እድሜ በላይ ላለ ሰው ብቻ ነው።ትልቅ ሰው ሲባል በሃሳቡ መልካም ሲሆን እንጅ እድሜው 70 ቢሆንም መልካም ስራ ከሌለው፣ በማስታረቁ፣በሃይማኖቱ የተሻለ ሰው ሲሆን ማለት ነው።ከ45 ዕድሜ በታች ሆኖ በስራው የሚታወቅ ከሆነም ይከወናል።

አቅራሪ፦ጎራው ና ጎራውና ጎራው ና እረ ጀኛው ናና

ተቀባይና ፈካሪ፦እንዲያ በል

አቅራሪ፦የእገሌ እናት ተይው አታልቅሽ፣(2)

የልቡን ሰርቶ ነው የሞተው ልጅሽ።

ተቀባይ እና ፈካሪ፦እውነት ነው እንዲያ በል አንተ …

በማለት አቅራሪውንም በተናገረው ስነቃል እያበረታቱ የሚለቀሰልተንም ሰው ያወድሱታል።ይህ ማለት ሟች ሰው ያሰበውን ምኞቱን፣የቤተሰቡን ህልም ፈፅሞ አርፏል ማለት ነው።

አቅራሪ፦የእገሌ እናት ላይ ላዩን እለፊ፣(2 ጊዜ)

እዚያ ወድቆልሻል ያሞራው ትራፊ።

ይህን ስነቃል የሚናገሩት የሞተው ሰው ገድሎት ሞቶ ከተገኘ ነው።ያሞራው ትራፊ ማለት ገዳዩን ሰው ሲነኩ ነው።አሞራ ክፉ ነውና።እንደነዚህ አይነት ስነቃሎች ሲነገሩ ሴቶች በጣም ያለቅሳሉ።እንዲህ እንዲህ እየሆነ ሲጥቀል ፍክራም በመሃል በመሃሉ አለበት።

ፎካሪ:-እስኪ ጀግና እንጥራ ተራ በተራ፣

እስኪ ጎበዝ ጥራ ተራ በተራ፣

እስኪ ትሁት ጥራ ተራ በተራ፣

እንዳትጨምረው ከፈሪ ሰው ጋራ።

ተቀባይ፦ እንዲያ በል እውነት ነው።

ፎካሪ፦ጋሽና ወርዶ ሲያንኮታኩተው፣

ዋሸራ ወርዶ ሲያንኮታኩተው፣

አድዋ  ወርዶ ሲያንኮታኩተው፣

ቱክ ብሎ ያያል ተኩስ የማያቅ ሰው::

በማለት ሚች ጀግና ተኳሽ መሆኑን ዪገልጻሉ::እንዲህ እየተባባሉ የለቅሶ ክዋኔውን ደመክመቅ ያደርጉታል::እንቅስቃሴው አቅራሪ ወደ ግራ ከሮጠ ፎካሪወች ወደ ቀኝ ይሄዳሉ::

## 3.3.3 ከተራኪ አንጻር

ትዉፊታዊ ትያትር ስርአት ባለው መልኩ እንዲቀጥል በቅደም ተከተል እንዲጓዝ ራሱን የቻለ ተራኪ አለው::በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ክዋኔም ስርአቱን ጠብቆ  እንዲጓዝ ራሱን የቻለ የለቅሶ አስተባባሪ አለው::በመጀመሪያ ክዋኔው ሲጀመር ጀምሮ ሁሉም ጸጥ ብሎ እንዲሰማ እና ጸሎት እንዲደረግ ከማድረግ አኳያ ከዚያ በኋላ ሴቶች ለቅሶውን በደረት ድቂ እንዲጀመር እና ወንዶችም ብረው በማስለቀስ እንዲጓዝ ያደርጋል::ከለቅሶ በኋላ ደግሞ የፍከራና ቀረርቶ ስርአቱ እንዲጀምር ወይንም የሚች የህወት ታሪክ ካለም እንዲነበብ የሚያደርግ ራሱን የቻለ ሰው አለው:: አቶ ቻሌ ታደሰ የጎንጂ ቆለላ ወረዳ ቅዱስ ገብርኤል ቀበሌ ነዋሪ ነው::የለቅሶ ስርአት ላይ አስተባባሪ ባይኖረው ምን ችግር ይኖረዋል?ብለን ጠይቀናቸው ዪህን ምላሽ ሰጥተዋል:: "ለቅሶ ላይ አስተባባሪ ከሌለው የህጻን ጭዋታ መሆኑ ነው::ሌላው ቀርቶ መስተንግዶ ላይ ንኳን በታም ይከብዳል::አስተባባሪ ከሌለው ምግቡ እንኳን ለሁሉም መድረሱን እና እንዴት መስተናገድ እንዳለበት ተነጋግሮ ለሰው በአሳወቅ በአግባቡ የሚያስሄድ ሲለሆነ እነዚህ መልካም መስተንግዶወች እና መከባበሮች ይጠፋሉ::ለቅሶው ላይ የሂወት ታሪክ የሚነበበው ቀረርቶና ፍከራ ሲጀምር ነው::ይህን ታሪክ ለቅሶው ላይ ቢያነበው ማንም አይሰማው እንዲሁ ዪቀራል:: "በማለት ተናግረዋል::

## 3.3.4 ከመድረክ ቁሳቁስ አንጻር

ትውፊታዊ ትያትር መድረክ ላይ የሚጠቀማቸው ቁሳቁሶች የማህበረሰቡን ማንነት የሚወክሉ ናቸው::ይህ ማለት የሁሉን ማህበረሰብ ሳይሆን ትውፊታዊ ትያትር ለሚሰራለት ማህበረሰብ  ማንነቱን ይገልጻል ማለት ነው::በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ክዋኔ ጊዜ የሚጠቀሙት ቁሳቁሶች ባህላዊ ናቸው::የራሳቸውን ማንነት እና ባህል የሚገልጹ ናቸው::ወደ

ለቅሶው ቦታ ሲሄድ ሁሉም ጠላ በመያዝ ሲሄድ ጠላው የሚያዘው በቶፋ ነው።ከአፈር የተሰራ እንስራ ነው።ጠላ በጎንጅ ቆለላ ባህል ዋናው እና ተወዳጂ መጠጥ ነው፣ሃይል እና ጉልበት የሚሰጣቸው መጠጥ ነው።ጠላ የሌለበት ቤት ከቤት አይቆጠርም።ከአፈር የተሰራ እንስራ ነው። የለቅሶው ክዋኔ ሲያልቅ ምግብ የሚመገቡበት በዕቃ ሳይሆን ድሮ አባቶች ሲያስሄዱበት በነበረው በጭሮ ነው።ጭሮ ማለት የጎመን ገለባ ነው።ለምን በዚህ እንደሚጠቀሙ አቶ ሙጨየ ስንሻው እንዲህ ይገልጻሉ።”አብዛኛውን ጊዜ ለቅሶ የሚደረግባቸው ቦታወች ከመኖሪያ ቤት ራቅ ያሉ ስለሚሆኑ እቃ መሸከሙን ለማቃለል ተብሎ እና ድካሙን ለመቀነስ ተብሎ በጭሮ እንጠቀማለን።”በማለት ይገልጻሉ።ሌላው እንጀራውን ከቤት ወደ ለቅሶው ቦታ የሚወስዱበት እቃ በሰፌድ ወይንም በወራንታ ነው።ወራንታ ወይም ሰፌድ ማለት ሴቶች በሰበዝና ግራምጣ በመስፋት የሚሰሩት ባህላዊ ዕቃ ነው።በካህናት በኩል ከበሮ፣ጽናጽል፣መቋሚያ፣ጽንዓ እና ሌሎችንም ይጠቀማሉ።

## 3.3.5 ከገጸ ባህርያት አንጻር

ትዉፊታዊ ትያትር በርካታ ገጸ ባህርያትን ያሳትፋል።በአብዛኛው ደግሞ አስተኔ ገጸ ባህርያት ናቸው።አስተኔ ገጸ ባህርያት ደግሞ በንግግሩ በሚፈጠረው ችግርም ሆነ ደስታ ባለቤት እንደሆነ እና ተጽዕኖ ፈጣሪም እንደሆነ ማንነታቸው  በቀላሉ የተወቀ ነው።በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርአት እንዲሁ በርካታ ሰወች በስርዓቱ ይሳተፋሉ።ማንኛውም እድሜው ከ 20 አመት በላይ የሆነ ሰው በክዋኔው መሳተፍ አለበት።በዚህም ለመቆጠር የሚያስቸግር በርካታ ሰው ይሳተፋል።እነዚህ ሰወች ታድያ  በእንቅስቃሴያቸው ለሚቹ ምን እንደሆኑ፣በለቅሶው ምን ድርሻ እንዳላቸው፣በእንቅስቃሴያቸው እና በአለቃቀሳቸው የታወቁ ናቸው።ማንንም ሰው በለቅሶው ሲሳተፍ ወዳጅ ዘመድ ከሆነ ምርር ብሎ ያለቅሳል፣ በአለባበሱም ቢሆን ጥቁር ልብስ ይለብሳል። እንደው መድረስ ስላለበት የሚመጣው ደግሞ ከነም አይቀርብም ራቅ ቢሎ ይቆምል።ስለዚህ በክዋኔው የምገኙ ሰውች እንዲሁ በሁኔታቸው ማንነታቸው የታወቀ ነው።

## 3.4 የጎንጂ ቆለላ ወረዳ የመስቀል ስርዓት

በጎንጂ ቆለላ ወረዳ አብዛኛው የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነው።ስለዚህ መስቀል በዓልን በድምቀት ያከብሩታል።ከሌሎች በዓላት ለየት ተደርጎ ይከበራል።ከሌሎች በዓሎች በምን ይለያል?የሚለውን ጥያቄ በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የቅዱስ ገብርኤል በተክርስትያን አገልጋይ መርጌታ ዋለ የኔአለም እንዲህ ገልጸዋል።”መስቀል የሕይወታችን ቁልፍ ነው።ሌሎች በዓሎች ከዚህ ጋር በጣም ይለየዋል።ይህ በዓል ክርስቶስ ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ያሳየበት ነው።ራሱን

አሳልፎ ሰጦ የተሰቀለበት ነው።በዚህም እለቱን መድሃኒት ነው፣ሃይላችን ጠፍቶ የተገኘበት ቀን ስለሆነ ከሌሎች በዓላቶች ለየት ባለ መልኩ እናከብረዋለን።ሌሎች በዓሎች ተዕዛዝ ናቸው።ይህ ራሱን የሰጠበት ነው።"በማለት ገልጸዋል።

መስቀልን በዓልን ገና በዋዜማው ጀምረው ሌሊቱን በሙሉ በድምቀት ሲያከብሩ ያድራሉ። በየቤቱ ጥሬው፣ጠላው፣ቡናው ተዘጋጅቶ በዋዜማው በመስከረም 16 ተጀምሮ ጎረቤት ከጎረቤት እየተጠራራ በደስታ ያመሻሉ።በዋዜማው ምሽት እስከ አራት ሰአት ሙሉ ዝግጅቱ ቤት ውስጥ ነው።ወጣቶች በበኩላቸው ደቦታቸውን እሳት ለኩሰው በየሰፈሩ እየዞሩ "የአመት መብራት"እያሉ ቤት አስከፍተው በመግባት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን ያደርሳሉ።ደቦት ከሸምበቆ ዛፍ የሚዘጋጅ ነው።በግራምጣም ታስሮ እሳት ተለኩሶ እየተበራ ይሄዳል።በየቤቱ ሲገቡ የደቦቱን እሳት ሰው አይን ወንም ፊት በማስጠጋት "እንቆረቆባሽ ወይም እንቆረቆባህ"ይላሉ።እንቆረቆባሽ ወይም እንቆረቆባህ ማለት እንኳን አደርሰህ ማለት ነው።መላሹም "እንኳን አብሮ አደረሰን"በማለት ይመልሳል።እንቆረቆባህ/ሽ ማለት ምን ማለት ነው?ብለን ጠይቀን በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስትያን አገልጋይ ቀሲስ ታረቀኝ እንዲህ ገልጸዋል። "እንቆረቆባህ/ሽ የሚለው የቃሉ ትርጉም ከየት እንደመጣ በግልጽ ባይታወቅም በተለምዶ ወጣቱ ያመጣው ነው፣ይህም ማለት እንኳን አደረሰህ/ሽ ለማለት ነው።"በማለት ገልጸዋል።

ወጣቶች ከሰፈር ሰፈር ሲዞሩ "እዮሃ" በማለት እየተቀባበሉ እስቱን ወደ ላይ አድርገው በመያዝ ይዞራሉ።እዮሃ ማለት ምን ማለት ነው? በማለት ጥያቄ አቅርበናል። የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስትያን አገልጋይ ዲያቆን በላይ ዘለቀ እንዲህ ዩገልጻል።"እዮሃ ማለት እየው አየነው ማለት ነው።ይህም መስቀሉ ሲቆፈር በታየ ጊዜ እየው ታየ እየዋ ያሉት ነው።በአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ምስጢር የያዘ ቃል ነው።ዛሬም ወጣቱ  እዮሃ ወይንም እዩት መስቀሉ ተገኝቷል  እንዲሁም አብርቷል በማለት የሚለውን ለመግለጽ ነው።"በማለት ገልጾታል።እንዲህ እያሉ ሰፈሩን ካደረሱ በኋላ ሜዳው ላይ ደመራ ደምረው በምስራቅ በኩል እሳት አያይዘው ሲደሰቱ ያመሻሉ።ሴቶች ወጣቶች በዚህ እለት ተደብቀው ያመሻሉ።

በወረዳው ባህል መሰረት በመስቀል በዓል በዋዜማው ሚሽት ሴቶች "እንቆረቆብቅሽ"ሲባሉ እንደወንዶች "እንኳን አብሮ አደረሳችሁ ማለት አይፈቀድም።ያገባች ከሆነች "እገሌ ባሌ ይቀርቅርብኝ" ያላገባች ከሆነች ደግሞ" የገናው ባሌ ይቀርቅርብኝ' ማለት አለባት።ይህ አባባል በጎንጅ ቆለላ ባህል ሰረት እንዲህ የምትል ሴት እንደ ባለየ ትቆጠራለች ።በመስቀል በዓል ቀን ይህን ትላለች ሁሉም ወጣት ይስቃል እና በፍቅር ይቀላለዳሉ።ይህን የምትመልስ ሴት

ደመራውጋ አብራ ቡና እያፈላች፣እየተጫወተች በአንድነት ታድራለች።ያላለች ሴት በእሳት ለኩሰዋትም እንድትል ትደረጋለች።ካለዚያም ይህን ቃል ማለት የማይፈልጉ ሴቶች ገና ወጣት ሰፈር መዞር ከመጀመሩ በፊት በየዛፉ ወይም በየገደሉ ተደብቅውቆይተው ወጣት ወንዶች ደመራው ከተደመረበት ቦታ ሲሄዱ ቤቷ ትገባለች።ደመራው ላይ ሴቶችም ይመጣሉ።ደመራው ከተቀጣጠለ በኂላ ምንም ጥያቄ አይጠየቁም።ሁሉም በአንድነት እና በፍቅር ጠላውን፣ አረቂውን፣ጥሬውን እና ቡናውን በመብላት እና በመጠጣት አብረው ያመሻሉ።

## 3.4.1 የመስቀል ባእል ቅድመ ዝግጂት

በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ለመስቀል በዓል ያላቸው አክብሮት በጣም ከፍተኛ ነው።ለዚህም ገና ከሁለት ወር በፊት የተለያዩ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ።በዓሉን በጎጥ በጋራ ስለሆነ ከሁሉም ሰው ብር ይዋጣና ለበዓል የሚታረድ በሬ ተገዝቶ እንዲበላ ይደረጋል።እናቶች ደግሞ ጠላውን በማድረግ እና በማዘጋጀት፣ጠጅ በመጥመቅ ዝግጅት ያደርጋሉ።ወጣቶች በበኩላቸው በዓሉ ሲደርስ ሶስት ሳምንት ሲቀረው ለደመራው የሚሆን እንጨት በየ ሰፈሩ በመዞር ይሰበስባሉ። ሊላው በወጣቱ የሚጠበቀው የደቦት ማዘጋጀት ስራ ነው።ለደቦት የሚሆነው ሸምበቆ የሚባል ዛፍ እንደመሆኑ መጠን ሸምበቆውን ቀጥቅጠው እንዲደርቅ ያደርጋሉ።ሸምበቆ የሆነበት ምክንያት ከሌሎች ዛፎች በደንብ መንደድ የሚችል ስለሆነ እንጂ የተለየ ምክንያት የለውም። ከደረሰ በኂላ ገና በመስከረም አስራ አምስት ቀን ደቦቱ ታስሮ ተዘጋጅቶ ዩቀመጣል።በመስከረም አስራ ስድስት ደግሞ በበነጋው የበዓሉ እለት ወጥ የሚሰራበትን፣ጠላ የሚሾምበትን፣እንጀራ የሚቀመጥበትን እቃወች ተሰብስቦ ዩቀመጣል።እቃው ተሰብስቦ የሚቀመጥበት እራሱን የቻለ ሜዳ ላይ የተሰራ ቤት አላቸው።እዚህ ቤት ዉስጥ አስቀምጠው በቁልፍ ይዘጋሉ።

ወጣቱ ቀን ስድስት ሰአት ላይ መስከረን 16 ደመራው ይደመራሉ።ስድስት ሰአት የሆነበት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል የተሰቀለበት ሰአት ነው።ደመራው ሲደመር አንድ እንጨት መረት ተቆፍሮ ይተከላል።ሌሎች እንጨቶችን አስደግፈው ያቆሚቸዋል።አንድ መሆኑ አንድ አምላክነቱን ነው።ከላይ ከተተከለው እንጨት ላይ የመስቀል ምልክት ይደረጋል።ከላይ የመሆኑ አይሁድ ኢየሱስን ሲሰቅሉት ከላይ የመስቀል ምልክት አድረገው ነበር የዚያ ምሳሌ ነው።ሌሎች እንጨቶች ተደግፈው የመቀመጣቸው ደግሞ የሰው ልጅ አምላክን ተደግፎ እንደሚኖር ለመግለጽ ነው።መስከረም አስራ ስድስት ቀን ምሽት አንድ ሰአት ጀምሮ ሁሉም ሰው በየቤቱ የሚጠበቅበትን ዝግጅቶች የሚጨርሱበት እና ወደ በዓሉ ክዋኔ የሚሸጋገሩበት ነው።

### 3.4.2 የመስቀል በዓል ደመራ አለኳኮስ

በጎንጅ ቆለላ ወረዳ መስቀል በዓልን ገና በዋዜማው ጀምረው በድምቀት ያከብሩታል። ደመራ ደምረው እሳት በመለኮስ በጋራ ያከብሩታል።የደመራ አለኳኮስ ላይ እንደፈለገው አይለኮስም። ራሱን ያቻለ የአለኳኮስ ስርአት አላቸው።መጀመርያ ላይ ካህን ካለ ወይንም ዲያቆን ካለ ጸሎት ይደርጋል።ከዚያ ወጣቱ ከቤት ይዞት የመጣውን ደቦት እያበራ ሶስት ጊዜ ወደ ቀኝ ይዞራሉ።ሶስት ጊዜ ከተዞረ በኋላ በምስራቅ በኩል እሳቱ ይለኮሳል።በምስራቅ የሆነበት በክርስታና ሃይማኖት ተከታዮች ብርሃን ናት ተብሎ ይታመናል።እሳቱ በራሱ ሃይል እየነደደ ሁሉንም አቅጣጫ ያያይዛል።ከተያያዘ በኋላ ሁሉም ደመራውን ከበው በመቀመጥ ቡና እየተፈላ በደስታ በፍቅር ያመሻሉ።ዘፈን እና ፍከራ ብሎም ቀረርቶ የእለት ዋና የምሽት ማሳለፍያ ጭዋታወች ናቸው።በበነጋው ከደመራው የሚገኘውን አመድ እንደ እምነት ይቆጠራል።በዚህም ሁሉም ግንባራቸው ላይ በመስቀል ምልክት ይቀቡታል።ሁሉም ሰው በጧት በመምጣት በዓሉን ደመቅመቅ ያደርጉታል እንዱሁ ዉሎውንም በደስታ ያሳልፋሉ።

## 3.5 የጎንጅ ቆለላ የመስቀል በዓል ከትዉፊታዊ ትያትር ባህርያት አንጻር ሲፈተሽ

### 3.5.1 ከመቼት አንጻር

በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል በዓል ስነ ስርዓት የሚካሄደው ከሌሎች በተለየ መልኩ ነው።የሚለየውም ከብቶች በሚታገዱበት ሰፊ ቦታ ነው።አብዛኛወቹ በዓላት የሚከወኑት በቤት ዉስጥ ነው።የመስቀል በዓል ደግሞ የአንድ ጎጥ ሰወች በጋራ ተሰብስበው ከብቶችንም በመያዝ ሜዳ ላይ ያከብሩታል።ደመራ የሚደመረውም ለሰወች መቀመጫ እንዳይጠብ ሰፋ ያለ ቦታ ላይ ነው።በዚህም ሰወች ቦታ ስይጠባቸው ሰፋ ባለ ቦታ ይቀመጣሉ።ለጭፈራው እና ለፍከራው ሰፋ ያለ ቦታ ስለሚያስፈልግና ከብቶችም አብረው ሜዳቸው ላይ ይውላሉ። ለምን አደባባይ ወይም ሜዳ ላይ እንደሆነ ቀሲስ ታረቀኝ እንዲህ ዪገልጻሉ።"ጌታችን አምላካችን መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው በቀራንዮ አደባባይ ነውና፣መስቀሉ የተቀበረበት ሜዳ ላይ ነበር የዚህ ምሳሌ ነው።"በማለት ገልጽዋል።

### 3.5.2 ከመዝሙርና ዉዝዋዜ አንጻር

በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የመስቀል ስርዓት ሲካሄድ እንደ ሌሎች በዓሎች ዉዝዋዜና የራሱ ዜማወች አሉት።ወጣቶች እንደ ፍከራ ዜማ በማዜም "የመስቀል ለታ የጅንጉርጉሩ፣እንኳን ደነኛው ያብዳል እጉሩ።"እያሉ እየደጋገሙ ሲፈክሩ ይታያሉ።ይህን አባባል ወጣቱ ቢቻ ሳይሆን

ህጻናት ሳይቀሩ ይናገራሉ።በቀረርቶ ጊዜ የፈለጋቸውን ስነቃል ይደረድራሉ።በፍከራ ሰዓት ፈካሪ በመንበርከክ እና በመነሳት ደስታውን ይገልጻሉ።የሚወድቅ የሚነሳው ፈካሪውና ለመፈከር የሚዘጋጁት ሰወች ናቸው።አቅራሪው ደግሞ ከፍካሪ በተቃራኒው ይንቅሳቀሳል።ስነቃሎች ላይ ለመስቀል ተብሎ የተቀመጠ የለም፤እንዲሁ የተለመዱ ስነቃሎችን ይጠቀማል።በአብዛኛው በዚህ እለት የሚጠቀሟቸው ስነቃሎች አብሮነታቸውን የሚገልጹበትን ነው።

አቅራሪ፦ጎራው ና ጎራው ና ጎራው ና

ተቀባይ፦እንዲያበል

አቅራሪ፦ሁለት ወንድምማማች ወንዝ ለወንዝ ወረዱ፣

ሁለት ወንድምማማች ወንዝ ለወንዝ ወረዱ፣

ወንድም የሌለውን እንደበሬ ሊያርዱ።

ተቀባይ፡እንዲያበል አንተ።

እየተባባሉ አብሮነታቸውን እና ወንድምነታቸውን ያጠናክራሉ።የስነቃሉን ትርጉም ስነቃሎን የነገሩን የጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነውሪ አቶ እውነቱ አያሌው እንዲህ ገልጸውታል።"ዛሬ በመስቀል በዓል ብዙ ነን ማንም አይነካንም፣በፍቅር በአንድነት ተሰብስበናል ማንም አይደፍረንም፣ተንኮለኛ ቢመጣ እንኳን ከበዓሉ የማይሳተፈውን ብቸኛውን ያርዳል ማለት ነው። "በማለት ገልጸዋል።ፈካሪ ይቀጥላል።

ፈካሪ፦አይሸከሽክ ዉሃ በጎታ፣(2)

እረግ አጅሬ የወንድም ጌታ።በማለት አንድነታቸውን ይገልጻሉ።

በዜማው ደግሞ ሰፈር ከሰፈር በሚዞሩ ሰአት "እዮሃ እዮሃ እዮሃ"በማለት በጋራ እየተቀባበሉ በድምቀት ያከብራሉ።ስለዚህ ትውፊታዊ ትያትር በመዝሙርና ዉዝዋዜ እንደሚታጀብ ሁሉ የጎንጂ ቆለላ ወረዳ መስቀል በዓም እንዲሁ በዉዝዋዜ እና በመዝሙር የታጀበ ነው።

### 3.5.3 ከተራኪ አንጻር

ትውፊታዊ ትያትር በአብዛኛው ጽሁፎች ተቆራርጠው ስለሚጻፉ በቅደም ተከተል ይካሄድ ዘንድ ተራኪ ይጠቀማል።በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል ስርዓት ክዋኔ ጊዜ ከመጀመሪያው ከዋዜማው ጀምሮ እንዴት ማስሄድ እንዳለባቸው አንድ አስተባባሪ መርጠው ስርዓቱን በፊት ይመራል።በተለይ በወጣቱ በየቤቱ እንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ለማድረስ በሚዞሩበት ሰዓት በፊት ሆኖ ከየትኛው ቤት መሄድ እንዳለባቸው የሚመራ አንድ ሰው አለ።ቤት ገብተውም ለምን ያህል ደቂቃ መቆየት እንዳለባቸው የሚነግራቸው ተውካይ አላቸው።ደመራው ላይ ማን ማን መገኘት እንዳለበት የሚያወያይ አንድ ወጣት አለ።የሚቀር ሰው አለ ሳይሆን በአጽንኦት መነገር ያለባቸውን አባቶች ነው።በአጠቃላይ ጅምሩ እስከ ፍጻሜው እዮሃው ላይ አንድ ወጣት ተወክሎ በስርዓት እንዲጓዝ ያደርጋል።በዋናው እለት በመስከረም 17 ደግሞ ከአባቶች ሃሳብ ተነስቶ ስራው በዛ ያለ በመሆኑ አስተባባሪ ተብለው እስከ አምስት ሰወች ይመረጣሉ።እነዚህ ሰወች ክዋኔው በስርዓት እንዲካሄድ የሚያደርጉ ናቸው።

### 3.5.4 ከመድረክ ቁሳቁስ አንጻር

በጎንጅ ቆለላ ወረዳ በማህበረሰቡ በናፍቆት ከሚከበሩ በዓላት አንዱ መስቀል በዓል ነው። በቤተክርስታያን በኩልም እለቱን የተመለከተ ቅዳሴ ይቀደሳል።ታድያ በቤተክርስትያንም ሆነ በየራሱ የሆኑ ባህላዊ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ።በቤተ ክርስትያን በኩል እንደ ከበሮ፣ጽናጽል፣ መቋሚያ፣እና ሌሎችን ባህላዊ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ።ማህበረሰቡ ከበሮ ከቤተ ክርስትያን አምጥቶ ሳይሆን ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን እንስራውን በጠንካራ ኮሽኮሽ አፉን በመሸፈን እንደ ከበሮ ሲደልቁት ያድራሉ።ከበሮ በጠንካራ ኮሰኮሽ እና በጠንካራ ቆዳ ሲታፈን ሲለሚጮህ ነው።ቡና ሲፈላም እንዲሁ የፍንጃል ማስቀመጫ እና ቡና የሚወቀጥበት እቃወች ባህላዊ ናቸው።ፍንጃል ማለት በዘመኑ አጠራር ስኒ ማለት ነው።ቡናው ተፈልቶ ሲያልቅ የፍንጃሉ ማስቀመጫ እናቶች በእጃቸው ግራምጣ እና ሰበዝ በማያያዝ በሰፉት እቃ ይቀመጣል። ሰበዝ እና ግራምጣ ተንካራ ሳሮች ስለሆኑ ነው።ቡናው ሲፈላም የስኒው ማስቀመጫ ገንዳ ከ እንጨት በተሰራ ገንዳ ነው።የቡና ዱቄት ማስቀጫው ደግሞ አባቶች ከእንጨት በሚያዘጋጁት ሙቀጫ በተባለ እቃ ይወቀጣል።በጥሩንባ በኩልም እንዲሁ የብረት ሳይሆን ከሸምበቆ በማዘጋጀት ይጠቀማሉ።ሸምበቆ በየትም ቦታ የሚገኝ እፅዋት ነው እናም ወጭንም ለመቀነስ ነው።ወጥ ሲሰራም ከአፈር በተሰራ ሸክላ ድስት ይጠቀማሉ።ትውፊታዊ ትያትር ሲከወን ባህላዊ እንደሚጠቀም ሁሉ የመስቀል በአል እንዲሁ ባህላዊ ቁሳቁሶችን ይጠቀምቅል።

አልባሳት ላይ በአብዛኛው የሚጠቀሙት ባህላዊ ልብሶችን ነው።ማለትም እናቶች ከጥጥ የሚሰሩት ጋቢ እና ነጠላዎች፣እናቶች ደግሞ እረሳቸው ከጥጥ ፈትለው አሰርተው ቀሚስ ይለብሳሉ።በካህናት በኩል ልብሰ ተከህኖ ይለብሳሉ።ቤተክርስትያን የሚቀመጥ አልባስ ነው። ይህም ቅዳሴ ላይ ብቻ ነው።

## 3.5.5 ከገጸ ባህሪያት አንጻር

ትውፊታዊ ትያትር ሲቀርብ በርካታ ገጸ ባህሪያትን ያሳትፋል።በአብዛኛው ደግሞ አስተኔ ገጸባህሪያት ናቸው።አስተኔ ገጸ ባህሪያት ደግሞ ማንነታቸው ለተምልካች ቅርብ የሆኑ ናቸው። በጎንጂ ቆለላ ወረዳ የመስቀል በዓል ክዋኔ ጊዜም በርካታ ሰወች ተሳታፊወች ናቸው።መንዝ እሚችል ሰው ሁሉ ይሳተፍበታል።በዚህ ክዋኔ ታድያ ሁሉም ማለት እንችላለን አስተኔ ገጸ ባህሪያቶች ናቸው።ወጥ ገጸ ባህሪያቶች በዋናነት አስተባባሪወች ናቸው።በጭፈራው መሃል ላይ ሆነው የሚጫወቱት ናቸው።እነዚህ ታድያ ጭፈራ የሚችሉ እና ጭዋታ የሚያውቁ ሰወች ናቸው።ሌሎች አስተኔ ናቸው።እኒኝህ ደግሞ ዳር እና ዳር ሆኔው የሚያጨበጭቡት፣ የሚቀበሉት ናቸው።ይህን የምንለይበትም ራሳቸውን አስተዋውቀው ሳይሆን በሚጫወቱት ጭዋታ፣በእንቅስቃሴያቸው ፣በንግግራቸው የታወቁ ናቸው፣በወረዳው ባህል መሰረት ምንም ቅሬታ እንዳይፈጠ ሁሌም ይነገራል።አንድ ሰው ቂም ይዞ ከሆነ ከልቡ መጫወት አይችልም፤ ተክዞ ለብቻው ይቀመጣል።ካለዚያ ምንም የተፈጠረ ከሌለ እንደሌሎች በደስታ ይጫወታል።

# ምዕራፍ አራት

## 4.ማጠቃለያ

ትውፊት ማለት ማስተላለፍ ወይም መቀበል ነው።ይህም ስርዓት እና ደንብን፤ እምነትንና ሃይማኖትን ሊሆን ይችላል።በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ዋና ትውፊቶች የሆኑት የለቅሶና የመስቀል በዓል ስርዓቶች ናቸው።ሁለቱ ስርዓቶች ምንጫቸው ከቤተ ክርስትያን ነው።በለቅሶ ከሚከወኑት ክዋኔወች አንዷ የሆነው አልባስ ላይ ጥቁር ልብስ ይለብሳሉ።ክርስቶስን አይሁድ ያለበሱት ምስጢር ነው።የፍታት ጸሎትም እንዲሁ ሰው በቀን 7 ጊዜ ይጸልይ ስለሚባል ሰው ሲሞትም 7 ጊዜ የፍታት ጸሎት ይደረጋል።ለቅሶው ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ የሚደረጉ ስርዓቶች የቤተክርስትያን ምሳሌ አላቸው።መስቀል ሙሉውን ቤተክርስትያን ላይ የሚመለከት ነው።

በጎንጅ ቆለላ የለቅሶ ስርዓት አንድ ሰው በጠና ወይንም በብርቱ ከታመመ የንስሐ አባቱ ለተወሰነ ጊዜ አብሮት እንዲሆን ይደረጋል።ሀጥያት ካለ እንዲናዘዝ፥ሀብትም ካለ እንናዘዝ ነው። የንስ አባት የሚናዘዘውን ሀብት በወረቀት ፅፎ ያስቀምጣል።የታመመው ከሞተ በኑዛዜው መሠረት በእኩልና በተገቢወ መልኩ ለልጆች ያከፋፍላሉ።ለሞት የመጨረሻ ደረጃ ወይንም መተንፈስም መመልከትም ሲደክም ሬሳ ጠባቂ ተመርጦ ይጠብቃል።ይህም ከሞተ ለግነዛ እንዳያስቸግር ሰውነቱን በአግባቡ እንዲያደርጉት ነው።ከሞተ በኋላ ሬሳው በወይራ በውሐ ይታጠብና የፍታት ፀሎት ተደርጎ ተገንዞ ወደ ቤተክርስቲያን እየሔደ ሰባት ጊዜ የፍታት ፀሎት ይደገማል።ከቤት ጀምሮ እስከሚቀበር ድረስ በ አጠቃላይ ሰባት ግዜ ጸሎተ ፍታት ይደረጋል። ጉድጓድ ተቆፍሮ ግብአተ መሬቱ ከተፈፀመ በኋላ ሁሉም ወደ የቤቱ ተመልሶ የእዝን እንጀራ እና ይዘው ሟች ቤተሰብ በመሔድ ነፍስ ይማር ምግብ ተበልቶ ይለያያሉ።ከዚህ በኋላ ለአንድ ወር ያህል ጧት ጧት መቃብሩጋ ይለቀሳል።ሌላ ጊዜ የለቅሶ ቀንም በመቅጠር በስፋት ይለቀስለታል።ሰው ሲሞት የሟች ቤተሰብ ሴቶች ፊታቸውን በእጃቸው ይልጡታል።ሀዘናቸውን ለመግለፅ ታሶቦ ነው።

በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል ባዕል ስነ ስርአት በደምቀት ከሚከበሩና ከሚናፍቁ የአመት ባዕሎች አንዱ ነው።መስቀል ባዕል በተለይ በወጣቶች ደመራ በመደመር በየ ሰፈሩ እየዞሩ "እዮሀ"በማለት እንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እያስተላለፉ ባዕሉን ገና በዋዜማው ያደምቁታል።ደመራውን ከምሺቱ አራት ሰዓት እሳት በምስራቅ በኩል እሳት ለኩሰው ቡና

በማፍላት፥ጠላውን እና ጥሬውን በመዘካከር በደስታ ያመሻሉ።በምሺቱ ዙረሺ ሴቶች አይሳተፉም።ምክንያቱም ለሴቶች "እዮሀ" እያሉ ሲዞሩ "እንቆረቆባሺ" ሲሉ የገናው ባሌ ይቀርቅርብኝ ብለው ካልመለሱ በእሳት ሲለሚለኩሷቸው ተደብቀው ስለሚያድሩ ነው።መልሱን በትክክል የመለሰ አብሮ በመዞር በሗላም ቡና ያፈላሉ።በአለቱ በመስከረም 17 ደግሞ የጎጡ ሰው በሙሉ ተሰብስቦ በሬ ታርዶ ፥ጠላውን፥እንጀራውን አምጥተው ላይ በፍቅር እና በመተሳሰብ በአንድነት ያከብሩታል።ባዕሉ የድህነት ባዕል በማለትም ያከብሩታል።

## የመፍትሔ ሀሳቦች

አንደኛ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ በለቅሶ ስርዓትውስጥ በርካታ አጉል ባህሎች አሉ።ሁሉም ማህበረሰብ የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች እንደመሆናቸው አንድ ሰው ሲሞት ሶስት ጊዜ ብቻ ይለቀሳል የሚል የሀይማኖት አስተምህሮም አላቸው።አንደኛ ሲሞት፥ሁለተኛ፥ሬሳ ከቤት ሲወጣ፥ ሶስተኛ ግብአተ መሬት ወይንም ሲቀበር የሚል ነው።ስለዚህ ለአንድ ሰው አንድ ወር ሙሉ ማልቀሲ መስተካከል ይኖርበታል።ወጭ ላይም ሰው ሲሞት ድግስ ይደገሳል።ይህም በአግባቡ መሆን አለበት።በተጨማሪም የቀጠሮ ለቅሶ ምንም አስፈላጊ ሆኖ አልታየኝምና መስተካከል ይኖርበታል በማለት አጥኝው አስቀምጧል።

ሁለተኛ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ማህበረሰብ ታላቅ ክብር ከሚሰጣቸው የአመት ባዕላት አንዱ የመስቀል ባዕል ሲሆን አሁን ላይ ደግሞ ብዙ ስርዓቶች እየተዘነጉ ነው።አብዛኛው ወጣቱ ደመራ ባዕሉ ላይ አለመገኘት እና የሚገኙትም በሚለኩሱ ሰዓት በፈለጋቸው አቅጣጫ እየለኮሱ ከክርስትና አስተምህሮ ትርጉሞች እየወጣ ስለሆነ የጎንጂ ቆለላ ወረዳ ቤተክህነት ሀላፊወች በትምህርት ስርዓቱን እንዲያስቀጥሉ ቢያደርጉ ጥሩ ነው።በየ አመቱ በየ ሰፈሩ እየተዞረ እዮሀ ይባል የነበረው ሁሉ ዛሬ ላይ እየቀነሰ በመምጣቱ ከማህበረሰቡ ፍቅርና አንድነት እየራቀ ስለሆነ ባህልና ቱሪዝም ከቤተ ክህነቱ ሀላፊወች ጋር ተነጋግሮ በዓሉን በድምቀት እንዲቀጥል ቢደረግ መልካም ነው በማለት አጥኝው ሃሳቡን አስቀምጧል።

# ዋቢ መጽሃፍት

ሊቀ መዘምራን ላእለ ማርያም ወልደ እየሱስ::መጽሃፈ ስንክሳር፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 2007ዓ.ም

መምህር ፍቅረ ማርያም::መጽሃፈ ታሪክ፤አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 1999 ዓ.ም

መቅደስ ሞገስ::የፋጫሳ አምልኮት ስነ ስርዓት ከትውፊታዊ ትያትር አላባውያን አንጻር፤ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፤2011 ዓም

በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር::መጽሐፍ ቅዱስ፤አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤2009ዓ.ም

አበበ ማስረሻ::የወገራ ወረዳ ፉከራ ከትውፊታዊ ትያትር አላባውያን አንፃር፤ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፤2012ዓ.ም

አበበ ግርማየ::የደመር ግራግንቦ የግጭት አፈታት ስርዓት ከተውኔት አላባውያን አንጻር፤ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፤2011ዓ.ም

ደበበ ሰይፉ::የትያትር ጥበብ፤አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤1973ዓ.ም

ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ::መድሎተ ጽድቅ ቁጥር 2::አዲስ አበባ ኢትዮጵያ::2012ዓ.ም

ፋንታሁን እንግዳ::ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔወቻቸው፤አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ 1993ዓ.ም

ዘሪሁን አስፋው::የስነጽሁፍ መሰረታውያን፤አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤2009 ዓ.ም

## ቃለ መጠይቅ የተደረጉ ጥያቄወች

1. የጎንጅ ቆለላ ወረዳ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እንዴት ነው?

2 .በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ሬሳ የሞተ ሰው ሲገነዝ የአገናነዝ ስርአት ላይ እንደየሰው ይለያል።ይህ ከምን አንጻር ነው?

3 .ጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ሬሳ ሲገነዝ ሲል በወይራ ቅጠል ይታጠባል ይባላል። በወይራ ቅጠል የሚታጠብ ለምን ነው?ከሌሎች ዛፎች በምን ዬለያል?

4.በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የለቅሶ ስርዓት ሲካሄድ ሰፊ ቦታ ያስፈለገበት ምክንያት ምን ምን ነው?

5.በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል በዓል ስርዓት ከሌሎች በዓል በተለየ መልኩ በድምቀት

ይከበራል።ከሌሎች በዓሎች በምን ይለያል?

6. .በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል በዓል ስርዓት እንቆረቆባህ/ሽ ማለት ምን ማለት ነው?

7. .በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የመስቀል በዓል ስርዓት እዮሃ ማለት ምን ማለት ነው?